Adda Demokraatawaa Oromoo — Oromo Democratic Front

*Bilisummaa fi haqa ummataa hundaaf!* — *Freedom and justice for all!*

**የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ) መግለጫ**

**ግንቦት 5፣ 2010 ዓም**

የኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ ልኡካን እና የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር አመራር አባላት በሀገሪቷ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየተስተዋሉ የመጡ የማሻሻያ ለውጦችን አስመልክቶ ከግንቦት 3-4፣ 2010 ዓም ውይይት ኣካሄደዋል። የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር በቆየ ፅኑ አቋሙ በመመስረት እነዚህ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲሰፉ፣ እንዲገለብቱና ፣ ጥልቀት እንዲኖራቸው ያለውን ፍላጎት በድጋሚ ያረጋግጣል። የኢትዮጵያ መንግሥት ልኡካን በበኩሉ በሰላማዊ መንገድ ከሚታገሉት ሁሉ ጋር ለመወያየትና ለመደራደር ያለውን ዝግጅትና ቁርጠኝነት ኣብስሯል።

ሁለቱም ልኡካን ከኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ) ጋር የተጀመረው ውይይት ለሰፊ ውይይት ፈር ቀዳጅ መሆኑን ኣስምረውበታል። ገና ብዙ የሚቀር ቢሆንም፣ ኦዴግ በቅርቡ በኢትዮጵያ መንግሥት በተወሰዱት የማሻሻያና የለውጥ እርምጃች ተበራቷል። በዚህም መሠረት እውነተኛ ፍትሓዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሃገራችን ዕውን እንዲሆን የሚመኙ በሃገር ቤትም ሆነ በውጪ ለለውጥ የሚንቀሳቀሱ ሁሉ የትግል ሥልታቸውን እንዲመረምሩና ትግላቸውን በሰላማዊ መንገድ ብቻ ለማካሄድ እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪ ያቀርባል።

ኦዴግ የተጀመሩት የማሻሻያና የለውጥ እርምጃዎች እንዲጎለብቱ ለማስቻል የሚጠበቅበትን ሚና ለመጫወት ዝግጁ መሆኑን ያበስራል። ይህንንም ለማሳካትና ውይይቱንም ለመቋጨት አንድ የኦዴግ ከፍተኛ ልኡካን በቅርቡ ወደ ሃገርቤት ያመራል።

ፍትህና ዴሞክራሲ ለሁሉም!

የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ)